9ኛ ዓመት ቁጥር 34
9th Year No. 34

ባህር ዳር ሐምሌ 13 ቀን 1996 ዓ/ም
Bahir Dar, July 20, 2004

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ህግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State
in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 17.82
Unit price 17.82

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 109/1996 ዓ.ም.
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤቶች ልማት ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ

Content

Proclamation No. 109/2004
The Amhara National Regional State Agency for the Development of Houses Establishment Proclamation

አዋጅ ቁጥር 109/1996 ዓ.ም.

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤቶች ልማት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በክልሉ ውስጥ በየጊዜው እያደገ የመጣውን የቤት ፍላጐትና አቅርቦት አለመጣጣም ችግር ለማቃለል የሚያስችለውን ምቹ የነፃ ኢኮኖሚ ሥርዓት በቤት ልማት ዘርፍ ማስፈን አስፈላጊ በመሆኑ፣

የክልሉ መንግስት በአዋጅ ቁጥር 47/1967 መሠረት የተወረሱትንም ሆነ አዲስ አሠርቶ በባለቤትነት የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች ሕንፃዎችና መጋዘኖች በሽያጭ ወደ ግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ዘርፍ ማስተላለፍ በማስፈለጉ፣

ከዚህ ቀደም በአመዛኙ ቤቶችን የማስተዳደርና የመገንባት ተግባርና ኃላፊነት ይዞ በአዋጅ ቁጥር 14/1988 እንዲቋቋም የተደረገው የክልሉ ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ለቤቶች ልማት የተሻለ በሚያግዝ ሁኔታ በአዲስ መልክ እንዲደራጅ በማድረግ አዳዲስ ግንባታዎችን በሰፊው ማካሄድ፣ ለተጠቃሚዎች በሽያጭ ማስተላለፍና በስሩ ያሉትን ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ እያሻሻለ ወደ ግል ባለቤትነት እንዲዛወሩ ለማድረግ የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፣

Proclamation No. 109/2004

A Proclamation Issued to Provide for the Establishment of an Agency for the Development of Houses in the Amhara National Regional State

WHEREAS, it has become necessary to prevail conducive free economic system in the sector of housing development which makes it possible to alleviate the ever growing unmet houses demand and supply in the Region;

WHEREAS, it is necessary to transfer houses, buildings and stores, which the Regional Government forfeited pursuant to Proclamation No. 47/1975 as well as those it has newly constructed and administered in ownership through selling to the private economic sector;

WHEREAS. it is deemed necessary to create conducive condition in order for the Regional Agency for the Administration of Rented Houses, which was to have been previously established under Proclamation No.14/1996 having significant duties and responsibilities of houses administration and construction, be newly organized in a way to make it better support housing development through massively undertaking new constructions, transfer same by selling to users and as may be necessary improve the quality of houses under its ownership and transfer same to promote ownership;

የድርጅቱን ተልዕኮ አሁን ልንከተለው ከሚገባን ኢኮኖሚያዊ ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ አቅጣጫ አንፃር በመቃኘትና ለዚሁ ተልዕኮ የሚያበቃውን አቅም በመገንባት በአዲስ መልክ ቀርጾ እንደገና ማቋቋም ተገቢ ሆኖ ፣በመገኘቱ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ና ንዑስ አንቀጽ 12 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የቤቶች ልማት ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 109/1996 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ቢሮ " ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ንግድ፣ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ነው።

2. "ቦርድ " ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመው የቤቶች ልማት ድርጅት ሥራ አመራር ቦርድ ነው።

ክፍል ሁለት
ስለድርጅቱ መቋቋም፣ ተጠሪነት አወቃቀርና ስልጣን

3. ስለድርጅቱ መቋቋምና ተጠሪነት

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤቶች ልማት ድርጅት /ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው መንግሥታዊ የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

WHEREAS, it is found proper to reestablish the Agency in a new form by shaping the Agency's mission with respect to the economic, social and political direction which we have to currently adhere and through building the capacity required for such mission;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region, in accordance with the power vested in it under the provisions of Article 49 Sub-Article 3/1/ and Sub- Article 12, hereby issues this proclamation.

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

This proclamation may be cited as "The Amhara National Regional State Agency for the Development of Houses Establishment Proclamation No109./2004."

2. Definitions

In this proclamation, unless the context requires other wise:

1. "Bureau" means the Amhara National Regional State Trade, Industry and Urban Development Bureau.

2. "Board" means the Managing Board of the Agency for Houses Development established pursuant to this proclamation.

PART TWO
Establishment, Accountability and Structure of the Agency

3. Establishment and Accountability of the Agency

1. The Amhara National Regional State Agency for the Development of Houses /herein after referred to as "The Agency"/ is hereby established as public enterprise being independent and having juridical personality as per this proclamation.

2. ድርጅቱ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ሆኖ ተጠሪነቱ ለቢሮው ይሆናል::

4. የድርጅቱ አላማ

የድርጅቱ ዓላማ ለመኖሪያና ለንግድ አገልግሎት የሚውሉ ቤቶችን በመገንባትና ለሽያጭ በማቅረብ፣ በተበዳሪዎች ጥያቄ ለቤቶች ልማት የሚውል ፋይናንስ በማደራጀት፣ በይዞታው ሥር የሚገኙ ቤቶችን በማስተዳደርና እንዳስፈላጊነቱ አሻሽሎ ወደ ግል ባለቤትነት እንዲዛወሩ ወይም እንዲተላለፉ በማድረግ በክልሉ ውስጥ የቤቶችን ልማት ማስፋፋት ነው::

5. የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት

የድርጅቱ ዋና መ/ቤት በባሕር ዳር ከተማ ውስጥ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች የሚቋቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል::

6. ድርጅታዊ አቋም

ድርጅቱ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል:-

1. የሥራ አመራር ቦርድ፣
2. ሥራ አስኪያጅ እና
3. አስፈላጊ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች::

7. የድርጅቱ ስልጣንና ተግባር

ድርጅቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ አዳዲስ የመኖሪያና የንግድ ቤቶችን ይሰራል፣ይሸጣል፣
2. የነባር ቤቶችን ዋጋ አተማመንና አሻሻጥ ሁኔታ አጥንቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም የሽያጩንና የማስተላለፉን ተግባር ያከናውናል፣

2. The Agency, being established for unlimited period of time, shall be accountable to the Bureau.

4. Objective of the Agency

The objective of the Agency is to expand the development of houses through constructing houses employed for dwelling and trading services, organizing finance upon the request of creditors for houses development, administering houses found in its possession and, as may be necessary, improving same and transferring or passing down to private ownership.

5. Principal Office of the Agency

The principal office of the Agency shall be in Bahir Dar and, as may be necessary, it shall have branch offices to be established in other places.

6. Organizational Structure

The Agency shall have the following bodies:

1. a Managing Board,
2. a manager; and
3. necessary heads and employees.

7. Powers and Duties of the Agency

The Agency, shall pursuant to this proclamation, have the following powers and duties:

1. as particulars to be determined by directive, construct and sell new dwelling and trading houses;
2. conduct studies on price determination and selling of former houses and thereby submit same to the Board and upon approval carry out the activity of selling and transferring thereto;

3. የቤቶችን ልማት ለማበረታታት የፋይናንስ አቅርቦት የሚገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

4. በከተሞች ውስጥ የቤቶች ግንባታ የሚቀላጠፍበትን በተለይም የመኖሪያ ቤቶች ቁጥር በስፋት የሚጨምርበትንና ነዋሪው ህብረተሰብ በአጭርም ሆነ በረጅም ጊዜ የቤት ባለቤት የሚሆንበትን ስልት እያጠና ለቦርዱ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

5. በይዞታው ስር የሚገኙትንና በየጊዜው የሚገነባቸውን ቤቶች ያከራያል፣ ያስተዳድራል፤

6. በስሩ የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች ኪራይ ተመንና የኪራይ ስሪት በየጊዜው እያጠና ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

7. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሣል፣ ይከሰሣል፤

8. ገንዘብ ይበደራል፣ ክፍያዎችን ይሰበስባል፤

9. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

ክፍል ሶስት
ስለድርጅቱ ስራ አመራር ቦርድ፣ስለስራ አስኪያጁና ስለቢሮው

8. ስለ ሥራ አመራር ቦርድ ምስረታና ተጠሪነት

1. በድርጅቱ ፖሊሲ ነክ ጉዳዮች ላይ መክሮ የሚወስንና ስራዎቹን በበላይነት የሚከታተል የሥራ አመራር ቦርድ /ከዚህ በኋላ "ቦርዱ " እየተባለ የሚጠራ/ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2. ቦርዱ ሰብሳቢውን ጨምሮ በቢሮው የሚሰየሙ አምስት አባላት ይኖሩታል።

3. የቦርዱ ተጠሪነት ለቢሮው ይሆናል።

3 facilitate conditions for securing financial provision for the encouragement of housing development;

4. study and submit to the Board a strategy by which the construction of houses in urban areas to be facilitated, and especially the number of dwelling houses is significantly increased and the residing community to be owner of houses in short or long period of time;

5. rent and administer houses under its possession and those it constructs each time;

6. study each time rent fee determination and rent tariff of houses in its administration, and implement same upon approval;

7. own property, enter in to contract, sue and be sued in its own name;

8. loan money and collect payment;

9. carry out other related activities required for the execution of its objectives.

PART THREE
The Managing Board of the Agency, the Manager and the Bureau

8. Establishment and Accountability of the Managing Board

1. A Managing Board /herein after referred to as "The Board"/, which deliberates and decides on policy related issues of the Agency and follows up its over all activities, is hereby established as per this proclamation.

2. The Board shall have five members designated by the Bureau.

3. The Board shall be accountable to the Bureau.

4. የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን ሶስት ዓመት ይሆናል። አስፈላጊ ሲሆን አንድ የቦርድ አባል የሥራ ጊዜው ሲያልቅ እንደገና ሊመደብ ወይም ሊሰየም ይችላል።

5. ለሥራው ተገቢ አለመሆኑ በበቂ ምክንያት ሲደገፍ አንድን የቦርድ አባል ቢሮው በማናቸውም ጊዜ ሊያነሣው ይችላል።

6. በድርጅቱ ስራ አስኪያጅ አቅራቢነት ቦርዱ የራሱን ድምፅ አልባ ፀሐፊ ይሰይማል።

9. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሠረት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ለድርጅቱ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

2. ድርጅቱ የሚጠናከርበትንና አሠራሩ የሚሻሻልበትን መንገድ ይቀይሣል፤

3. የድርጅቱን ሥራ አስኪያጅ ይቀጥራል፤ ደመወዝና አበሉን ይወስናል፣ ከሥራ ያሰናብታል፤

4. ለሥራ አስኪያጁ ተጠሪ የሆኑትን የሥራ ኃላፊዎች ቅጥር፣ ምደባ፣ ዝውውር፣ ደመወዝና አበል ይወስናል፣ የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ማንዋል ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት መርምሮ ያፀድቃል፤

5. የድርጅቱን ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል እና ጥቅማጥቅሞች ይወስናል፣ የሠራተኞቹ አስተዳደራዊ ማንዋል ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት መርምሮ ያፀድቃል፤

6. የድርጅቱን መዋቅር ገምግሞ ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

7. የድርጅቱን የአጭር ጊዜ ዕቅድና በጀት መርምሮ ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል።

4. The term of office of the members of the Board shall be three years; where necessary, a member of the Board may be reassigned or redesignated when his term of office is over.

5. The Bureau may at any time discharge a member of the Board when he is proved to be inappropriate for the job with sufficient reason.

6. The Board shall, upon the recommendation of the manager, assign its own no vote secretary.

9. Powers and Duties of the Board

The Board shall, pursuant to this proclamation, have the powers and duties indicated herein under:

1. follow up and control that the powers and duties vested in the Agency under Article 7 hereof are accurately implemented;

2. design ways for strengthening the Agency and improving its operation;

3. employ, determine salary as well as allowance of the manager of the Agency; and dismiss same;

4. determine employment, assignment, transfer, salary and allowance of those heads accountable to the manager; and approve the administrative manual for the heads when prepared and submitted to it;

5. determine salary scale and benefits of employees of the Agency; examine and approve administrative manual of the employees when prepared and submitted to it;

6. approve and improve structure of the Agency upon evaluation; follow up the implementation of same;

7. approve short term plan and budget of the Agency and thereby follow up the execution of same;

8. የድርጅቱ የሥራ ንንስና የንብረት አስተዳደር መመሪያ ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት መርምሮ የፀድቃል ፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

9. የቦርዱን ፀሐፊ ዝርዝር የስራ ሀላፊነትና አበል ይወስናል፤

10. የቦርዱንና የድርጅቱን አጠቃላይ የሥራ አፈፃፀም በተመለከተ ወቅታዊ ዘገባዎችን ለቢሮው ያቀርባል።

10. ስለቦርዱ ስብሰባና ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፤ ሆኖም በቦርዱ ሰብሣቢ ጥሪ ወይም ከቦርዱ አባላት መካከል አንድ ሰስተኛዎቹ ከጠየቁ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

2. ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤

3. ቦርዱ ማናቸውንም ውሣኔ የሚያሣልፈው በድምፅ ብልጫ ሲሆን ድምፁ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሣቢው የደገፈው ሃሣብ የቦርዱ ውሣኔ ሆኖ ያልፋል፤

4. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን ዝርዝር የስብሰባና ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

11. የሥራ አስኪያጁ ስልጣንና ተግባር

1. የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን ስራውን በበላይነት ይመራል፣ ድርጅቱን ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራ አስኪያጁ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ስር ለድርጅቱ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ከማስፈጸም በተጨማሪም የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

8. approve the financial and property administration guideline of the Agency when prepared and submitted to it; follow up the implementation of same;

9. determine specific job responsibility and allowance of the secretary of the Board;

10. submit periodic report to the Bureau concerning the over all performance of the Board and the Agency.

10. Meeting and Internal Working Procedure of the Board

1. The Board shall convene its regular session once a month; extra ordinary session, however may be convened in any time upon the request of the chairperson of the Board or one-third of members of the Board.

2. There shall be a quorum where more than half of the members of the Board are present at its meeting.

3. Any decision of the Board shall be passed by majority vote; in case of a tie, however, the chairperson shall have a casting vote;

4. Without prejudice to the provision provided in from Sub-Article 1 to 3 of this Article, the Board may draw up its own internal rules of meeting and working procedure.

11. Powers and Duties of the Manager

1. The Manager of the Agency shall, being the chief executive of the Agency, direct over the activity of the Agency, administer and control same;

2. Without prejudice to the generality of Sub-Article 1 of this Article, the manager shall discharge specific duties given to the Agency under Article 7 of this proclamation and the following as well:

3. ሥራ አስኪያጁ ለድርጅቱ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገው መጠን ሥልጣንና ተግባራቱን በከፊል ወይም በሙሉ ለበታች የስራ ኃላፊዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

4. ሥራ አስኪያጁ በማይኖርበት ወቅት ተክቶ የሚሠራውን ሰው ከ30 ቀናት በላይ ለሚሆን ጊዜ የሚወክል ከሆነ ውክልናውን አስቀድሞ ለቦርዱ በማቅረብ ሚስፀደቅ ይኖርበታል።

12. የቢሮው ስልጣንና ተግባር

በአዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም. /እንደተሻሻለ/ና በሌሎች ሕጐች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው፡-

1. የቦርድ አባላትን ይሰይማል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፤

2. በቦርዱ የሚቀርቡለትን የድርጅቱን የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅዶች፣ ዓመታዊ ግቦችና አላማዎች ያፀድቃል፤ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፤

3. ለቦርዱ ሰብሣቢና ለአባላቱ ሊከፈል የሚገባውን አበል ይወስናል፤

4. የድርጅቱን የተስተካከለ የንብረት ዋጋ ግምት መርምሮ ያፀድቃል፤

5. የውጭ አዲተሮችን በመሰየም የድርጅቱ ሂሣብ እንዲመረመር ያደርጋል፣ የሚቀርብለትንም የሂሣብ ሪፖርት መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል፤

6. ለቦርዱ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉን መንግሥት የባለቤትነት መብት ለማስከበር የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

3. The manager may delegate his powers and duties in part or in full to subordinate heads of the Agency to the extent required for the expedition of the activities of the Agency.

4. Where the person to act in the absence of the manager is delegated for more than 30 days, the prior approval of the delegation by the Board shall be required

12. Powers and Duties of the Bureau

The Bureau, without prejudice to the powers and duties vested in it with Proclamation No. 60/2001/ (as amended) and other laws, shall:

1. assign members of the Board and follow up their activities;

2. approve medium and long term plan, annual goals and objectives of the Agency submitted to it by the Board; follow up the implementation of same;

3. determine the allowance to be paid to members and chairperson of the Board;

4. examine and approve the evenly estimated value of property of the Agency;

5. cause the account of the Agency to be audited by assigning external auditors, examine the audit report submitted to it and render decision thereon;

6. without prejudice to the power and duties vested in the Board, carry out other duties necessary to ensure ownership right of the Regional Government.

ክፍል አራት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. የድርጅቱ ካፒታልና የበጀት ምንጭ

1. ለጊዜው ከይዞታው ውጭ የሆኑና የተረጋገጡ ሃብቶችን ተከታትሎ የማስመለስ መብቱን ተፈፃሚ ሲያደርግ በካፒታሉ ጣሪያ ላይ የሚኖረው ለውጥ እንደተጠበቀ ሆኖ የድርጅቱ የተከፈለ ካፒታል ብር 158,224,574.34/አንድ መቶ ሃምሳ ስምንት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃያ አራት ሺህ አምስት መቶ ሰባ አራት ብር ከሰላሣ አራት ሣንቲም/ ነው::

2. ድርጅቱ ከሚከተሉት ምንጮች ተጨማሪ ካፒታል ሊያገኝ ይችላል:-
   ሀ. የክልሉ መንግስት ግምጃ ቤት፣
   ለ. የባንክ ብድርና
   ሐ. ሌሎች ምንጮች

14. የበጀት ዓመት

የድርጅቱ የበጀት ዓመት የክልሉ መንግስት የሚሠራበት የበጀት ዓመት ይሆናል::

15. ስለመጠባበቂያ ሂሣብና የትርፍ አደላደል

የድርጅቱ የተመረመረና የተጣራ ትርፍ አደላደልና የመጠባበቂያ ሂሣቦች ጉዳይ የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

16. ስለሰው ኃይል ቅጥርና አስተዳደር

የድርጅቱ ሠራተኞች ቅጥርና አስተዳደር በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግ መሠረት ይፈፀማል::

17. የሂሣብ መዛግብት

1. ድርጅቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል፣

PART FOUR
Miscellaneous Provisions

13. Capital and Budget Sources of the Agency

1. Without prejudice to the change upon the capital ceiling of the Agency while enforcing its right to follow up and recover properties which are out of its possession and those ascertained thereof, the paid up capital of the Agency shall be 158,224,574.34(One Hundred Fifty Eight Million Two Hundred Twenty Four Thousand and Five Hundred Seventy Four Birr and Thirty Four Cents).

2. The Agency may gain additional capital from the following sources;
   a. Regional Government Treasury;
   b. Bank Loan; and
   c. Other Sources.

14. Budget Year

The budget year of the Regional Government shall be the budget year of the Agency.

15. Reserve Accounts and Allocation of Profit

The issue of audited and net profit allocation as well as reserve account of the Agency shall be determined by a directive to be issued by the Regional Finance and Economic Development Bureau.

16. Employment and Administration of Human Resource

Employment and administration of employees of the Agency shall be executed pursuant to the Labor Law.

17. Books of Account

1. The Agency shall keep complete and accurate books of account.

2. በሂሣብ መዛግብቱና በገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶቹ አያያዝና አጠባበቅ ረገድ ድርጅቱ ተቀባይነት ያላቸው የድርብ ሂሣብ አሠራር መርሆዎች ይጠቀማል።

18. የሒሣብ ምርመራ

የድርጅቱ ሂሣብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና አዲተር መ/ቤት ወይም ቢሮው በሚሰይማቸው የውጭ አዲተሮች ይመረመራሉ።

19. የድርጅቱ የንግድ ምልክት

ድርጅቱ የክልሉን መንግስት ፖሊሲና መልካም ስነ-ምግባርን እንዲሁም የሶስተኛ ወገኖችን መብት የማይቃረን የንግድ ምልክት ይኖረዋል።

20. ስለድርጅቱ መፍረስ

ድርጅቱ ከሚከተሉት ምክንያቶች ባንዱ ሊፈርስ ይችላል፦

1. የተቋቋመበት አላማ ከተፈፀመ፤
2. ድርጅቱ የተቋቋመበት አላማ መፈጸም የማይችል ሲሆን፤
3. የድርጅቱ መክሰር በፍርድ ቤት ሲወሰን።

21. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

በአዋጅ ቁጥር 14/1988 ዓ.ም. /እንደተሻሻለ/ የተቋቋመው የአማራ ብሔራዊ ክልል ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት መብትና ግዴታ በዚህ አዋጅ ወደ ተቋቋመው ድርጅት ተላልፏል።

22. የኃላፊነት ወሰን

ድርጅቱ በዕዳ ተጠያቂ የሚሆነው ያለው ጠቅላላ ንብረት እስከሚሸፍነው ድረስ ብቻ ይሆናል።

2. The Agency shall employ acceptable double entry system principles with regard to the keeping and maintaining of books of account and financial as well as property related documents.

18. Auditing

Books of account and financial as well as property related documents of the Agency shall be audited by the Office of the Auditor General of the Region or by external auditors assigned by the Bureau.

19. Trade Mark of the Agency

The Agency shall have a trademark having no contradiction with the policy of the Regional State, good ethics as well as rights of third parties.

20. Dissolution of the Agency

The Agency shall be dissolved in one of the following reasons:

1. upon the accomplishment of its establishment objective;
2. where the establishment objective of the Agency fails to be executed;
3. where the bankruptcy of the Agency is decided by court.

21. Transfer of Rights and Duties

The rights and duties of the Amhara National Region Rented Houses Administration Agency, established by Proclamation No. 14/1996 (as amended), is hereby transferred to the Agency established as per this proclamation.

22. Scope of Liability

The Agency shall be held liable only to the extent of its total assets.

23. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጐች

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 14/1988 ዓ.ም. /እንደተሻሻለ/ ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል።

2. ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ህግ፣ደንብ፣መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

24. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች የማውጣት ስልጣን አለው።

25. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ይህንን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ቢሮው ሊያወጣ ይችላል።

26. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባሕርዳር
ሐምሌ 13 ቀን 1996 ዓ.ም.

ዮሴፍ ረታ

የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዳንት

23. Repealed and Inapplicable Laws

1. The Amhara National Regional State Rented Houses Administration Establishment Proclamation No.14/1996 (as amended) is hereby repealed and replaced with this proclamation.

2. Any law, regulation, directive or customary practice inconsistent with this proclamation shall be inapplicable on matters provided in this proclamation.

24. Power to Issue Regulation

The Council of the Regional Government shall have the power to issue regulations necessary for the implementation of this proclamation.

25. Power to Issue Directive

Without prejudice to other provisions of this proclamation, the Bureau shall have the power to issue directives necessary for the implementation of this proclamation and regulations to be issued pursuant to this proclamation.

26. Effective Date

This proclamation shall come into force commencing its publication date in the *Zikre Hig Gazetta* of the Regional state.

Done at Bahir Dar,
This 20th day of July, 2004.

Yosef Retta

President of
the Amhara National Region